# የቴዲ አፍሮ የተቃውሞ ዘፈኖች

ዓለማየሁ አበበ

የማይነጋ ሕልም ሳልም፤
የማይድን በሽታ ሳክም፤
የማያድግ ችግኝ ስከረክም፤
እኔ ለኔ ኖሬ አላውቅም።[1]

ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን

ድምጻዊ[2] ቴዎድሮስ ካሣሁን (ቴዲ አፍሮ) በቅርቡ በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ ኢትዮጵያዊ[3] በመኪና ገጭተህ ገድለሃል በሚል በመንግሥት ክስ ከተመሰረተበት በኋላ በመንግስት የጥበቃ ሃይሎች ቁጥጥር ስር ውሎና በመንግስት ሙሉ ቁጥጥር ስር ባሉ ፍርድ ቤቶች ቀርቦ፤ መንግስት በሰየማቸው ዳኞች የስድስት ዓመት እሥራት ተፈርዶበት ወህኒ በተላከ ወቅት በሃገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሃገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ምላሽ የዚህን ጽሁፍ አቅራቢ ቀልብ መሳቡ ለዚህ ጽሁፍ ዝግጅት መነሻ ምክንያት ሲሆን ዓላማው በተለይ ባለፉት ሁለት አሠርት ዓመታት ውስጥ ጎልቶ የታየውን የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ትግል ሂደት ድምፃዊው በዘፈኖቹ እንዴት እንዳከተታቸውና ለትግሉም ያደረገውን አገዛ ከተቃውሞ የኪነጥበብ ዘርፍ አንፃር በጣም ባጭሩ ማሳየት ነው።

## ገጸብ፡

**በኢትዮጵያ "ድምፃዊ" የሚለው መጠሪያ አለመታደል ሆኖ "አዝማሪ" የሚል ስም ያተረፉትን፤ በኢትዮጵያ ቴአትር ቤቶች ተቀጥረው በሙያተኝነት ያገለገሉትንና በማገልገል ላይ የሚገኙትን፤ ከዚያም አልፎ ተርፎ ዕድለኛ ሆነው በዘመን አመጣሽ መቅረፀ-ድምጽ ዘፈኖቻቸውን አስቀድተው ለማሰራጨት የቻሉትንም ያልቻሉትንም የሚያጠቃልል የድንቅ ባለሙያዎች የጋራ መጠሪያ ነው። ሆኖም ይህ አጭር ጽሁፍ ተዝቆ የማያልቀውን የኢትዮጵያውያን ድምጻውያን ስራዎች ሁሉ አቅርቦ ትንታኔ አያደርግም። እንዲህ ዓይነቱን ተግባር ይህን መሰል ጠባብ መድረክ በበቂ ሊያስተናግደው የማይችል በመሆኑና አባይን በጭልፋ እንዳይሆን በማሰብ ጭምር ገደብ ተበጅቶለት በድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ይዘት በተለይም ላቀረባቸው ወቅታዊና ብሔራዊ የተቃውሞ መልዕክቶች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷል።[4]**

---

**ዓለማየሁ አበበ** ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ የመጀመሪያ ዲግሪውን በድህረ ምረቃ ትምህርት ፕሮግራም በስነልሳን ሁለተኛ ዲግሪውን አግኝቷል። በተማረበት ክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ ቋንቋና ስነጽሁፍ ነክ ኮርሶችን በማስተማር ለዘጠኝ ዓመታት አገልግሏል። ዓለማየሁ ከማስተማር ተግባራት በተጨማሪ አቅሙና ችሎታው በፈቀደ መጠን በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ላይ ያተኮሩ የምርምርና የጥናት ጽሁፎችን በሃገርቤትና በውጭ ሃገር በተዘጋጁ ብሔራዊና ዓለም አቀፍ ኮንፍረንሶች ላይ አበርክቷል። በ1993 ወደ ዩናይትድ ስቴትስ ከመጣ በኋላም በ1992 ጀርመን ሃገር ኮሎን ዩኒቨርሲቲ ጀምሮት የነበረውን የስነልሳን የዶክትሬት ዲግሪ የማሟያ ጽሁፍ ለሜሪላንድ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ክፍል በማቅረብና ተጨማሪ ኮርሶችን በመውሰድ በ1998 የዶክትሬት ዲግሪ ተቀብሏል።

---

The *International Journal of Ethiopian Studies* (ISSN: 1543-4133) is published two times a year by Tsehai Publishers. www.tsehaipublishers.com. Copyright © 2009. Volume IV, Number 1&2 (Double Issue).

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

## መንደርደሪያ፦

እንደብዙዎች የአፍሪካ ሃገሮች የኢትዮጵያም ዘመናዊ ሙዚቃ መነሻ የትውፊት[5] አንድ ክፍል የሆነው ባሕላዊ ኪነት ነው። ባሕላዊ ኪነት በዕድሜ ሳይቀር ረዘም ያሉ ዓመታትን ያስቆጠረ አንጋፋ የኪነጥበብ አንድ አካል በመሆኑ በዘመናዊ ሙዚቃ ዘርፍ የራሱ አሻራ የማኖር ዕድሉ ሰፊ ነው። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ሙዚቃ ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ ከመድረሱ አስቀድሞ በቃልም በግብርም ሲተላለፍ ካለንበት ወቅት ከደረሰው ባህላዊ ኪነት ማለትም የየብሄረሰቡ ረገዳ፣ ጭፈራ፣ ዝየራ፣ ሽለላ፣ ቀረርቶ...ወዘተ ጋር እየተዋዋሰና አንዱ አንዱን እያበለፀገ ረጅምና ሰፊ ጉዞ ተጉዟል። ባህላዊ ኪነትም ሆነ ዘመናዊው ሙዚቃ ታድያ እንደማንኛውም የኪነጥበብ ስራ መነሻና ምንጫቸው የየዘመኑ ነባራዊ ሕይወት ነውና ደራሲዎቻቸው ከየወቅቱ የኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ እየነቀሱ የሕዝቡን ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ገጽታዎች በማንፀባረቅ ረገድ ጉልሕ ሚና ተጫውተዋል። ይህን የኪነጥበብ ልዩ ድርሻ ሲያብራራ የስነጽሁፍ ባለሙያው ውድዎርድ ሮበርት (1965፡ 22-23) "…Art is a medium that enables the masses to easily grasp and form opinions on a subject, and as such has often been an instrument of significant value to leaders of protest movements. The manipulation of words and images has made literature one of the most successful means for expressing discontent with the status quo…" ሲል ገልፆታል።

በኢትዮጵያ አያሌ ብሔረሰቦች እንደመኖራቸው በሰርግ፣ በሞት፣ ባውዳመት፣ በእርሻ፣ በጉልጓሎ፣ በአረም፣ በውቂያ፣...ወዘተ ወቅቶች በዝርውም ሆነ በስንኝ እየተቋጠሩ በልዩ ልዩ ከያንያን በቃልና በግብር የተከወኑ የዘፈን ቅርጾች ለየተደረሱበት ብሔረሰብ ማዝናኛና ማስተማሪያ ሆነዋል። በአካባቢም ሆነ በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚታዩ በጎና ደካማ ጎኖች ለመግለጫ አገልግለዋል። እንዲያም ሲል የየወቅቱን የፖለቲካ ሥርዓትና የሥርዓቱን አራማጆች ተግባራት ጭምር በይፋ ለመቃወም የደፈሩ ይገኙበታል።[6]

ከስልሳ ስድስት በፊት የነበረውን ፊውዳላዊ የአገዛዝ ስርዓት ማንነት በይፋ ለመቃወም ወቅቱ ያልፈቀደለት የኢትዮጵያ አርሶ አደር፡-

ርሃቤ ጥማቴ እርዛኔ ሶስቱ፤
ይደበድቡኛል ባንድ እየዶለቱ።[7]

ሲል በማንጎራጎር የዘመኑን የጭቆና መጠን ብቻ ሳይሆን የመሰረታዊ ፍላጎቶችን እንኳ አለማሟላት በጥቂት ቁጥብና ምጥን ቃላት ፍንትው አድርጎ ለማሳየት ችሏል። በዚሁ ስርዓት የፊውዳል ባላባቶች ጭካኔ የተመላበት ድርጊት ያንገፈገፈው ገበሬ፡-

ጊዜ እንዲያልፍ ብዬ፤ የደላው መስዬ፤
ለምስለኔ ዳርኳት ምሽቴን እቴ ብዬ።[8]

በማለት ቁጭቱን ብቻ ሳይሆን የነበረበትን ዘመን አስከፊ ባሕርይና የአስተዳደሩን ብልሹነት በምሬት ለመግለጥ መገደዱ የባህላዊ ኪነትን ልዩ ሚና ቁልጭ አድርጎ ያሳያል።

የፊውዳሉን ስርዓት የተካው ወታደራዊ ደርግ ያለውድ በግድ ተግባራዊ ባደረገው የሰፈራ ፕሮግራም እጅጉን የተማረረውና ከወሎ ወደከፋ ክፍለ ሃገር እንዲዛወር የተገደደ የወቅቱ አፈር ገፊ ባንድ ወቅት በውጭ ሃገር የዕርዳታ እህል መማረሩንና በሰፈራው ፕሮግራም ቀድመው እንዲሳተፉ የተገፉ ወገኖቹ ለወባ በሽታ መዳረጋቸውን ለመግለጥ በውስጠ ወይራ፡-

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

የካናዳን ስንዴ በልቼ በልቼ፤
መሄዴ ነው ጅማ ሰርግ ተጠርቼ።[9]

ሲል ለሚጠብቀው አደጋ አስቀድሞ ሙሾውን አውርዶ ነበር።

ዛሬም በህወሓት/ኢሕአዴግ ዘመን በኢትዮጵያ ሰሜናዊ ክፍል "በእሪ በል ሰቆጣ፤ እሪ በል ኮረም" ዜማ አርሶ አደሩ፦ (ተስፋዬ ገብረአብ፣ የጋዜጠኛው ማስታወሻ፣ ገጽ 30-31)

አዲስ አዲሱ ሰው - በዝቶ እየተባዛ፤
ከባዶ ሜዳ ላይ - ቀረን እንደዋዛ።

........................................

ወልቃይት ፀገዴን - አስተውሎ ላያት፣
ወይ ያኔ ወይ ያኔ - ወይን ናት ወይን ናት።

........................................

ምንም ባንቀበር - ባንገባ መሬት፤
አያሳፍረንም - ሞተናል ማለት።

እያለ ለአያሌ ዓመታት ዕጣ ፈንታው የሆነውንና ዛሬም ያላቋረጠውን በደልና ጭቆና በመቃወም ላይ እንደሚገኝ በቅርቡ ለሕትመት የበቃ ዜና መዋዕላዊ ልቦለድ ይፋ አድርጎታል። በደልና ጭቆናውን ባደባባይ ቢገልጥ ሊደርስበት የሚችለውን አደጋና ብቻውን ሊጋፈጠው የማይችለውን ባለጋራ አስቀድሞ ጠንቅቆ በማወቅ ሰርክ ባህላዊ ኪነትን ጥላ ከለላ አድርጎ የተቃውሞ ድምፁን በማሰማት ብልጠት የኢትዮጵያን አርሶ አደር (ባጠቃላይ የገጠር ነዋሪውን ኢትዮጵያዊ) የሚስተካከለው የለም ቢባል ከቶም ማጋነን አይሆንም። ይህ ማለት ግን ከተሜው በዚህ ጥበብ የተካነ አይደለም ማለት አይደለም።

በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ሳያቋርጥ ለዘመናት የደረሰውና ዛሬም በመድረስ ላይ ያለው ግፍና መከራ በባህላዊ ኪነት መስክ ብቻ ሳይሆን በዘመናዊ ሙዚቃ ዘርፍም ሲንጸባረቅ የኖረ ሃቅ ለመሆኑ አያሌ ማስረጃዎች ማቅረብ ይቻላል። ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ድምጻውያን የኖሩበትን ዘመን ማኅበረሰባዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መስክ በጎና ደካማ ጎን በድፍረት ሲገልጡ ለመኖራቸው ስራዎቻቸው ቀዳሚ ምስክሮች ናቸው።

በአፄ ሃይለ ሥላሴ ዘመን ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ድምጻውያን በግልጽ ወቅታዊና አንገብጋቢ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ በድፍረት ያቀነቀኑትን ያህል ሁለንተናዊ ጭብጦችን እያስታከኩም በዘዴና በብልሃት የስርዓቱን ዋነኛ የጭቆና መልኮች ለማንጸባረቅ ደፍረዋል። በሃገራችን የሙዚቃ ታሪክ ልዩ ትዝታን አሳድረው ካለፉ ድምጻውያን መካከል ብዙነሽ በቀለ በአይደፈሬው ባላባትዊ ስርዓት ወቅት ነው፦

አያገባው ገብቶ ሰው ይዘባርቃል፤
እኔን ስሜን እንጂ ምኞቴን ማን ያውቃል።

..................................

ፎቅና ማርቸዲስ ስሜት አይሰጡኝም፤
እኔን ፍቅር እንጂ ሃብት አያሞኝኝም።[10]

እያለች ሃብትና ንብረት የ"ሰውነት" መለኪያ የነበሩበትን የፊውዳል ስርዓት ባደባባይ የሞገተችው።

ታዋቂው ድምጻዊ ጥላሁን ገሰሰ ዛሬ ኢትዮጵያ በዓለም ካርታ ላይ ሌላ ቅርጽ ይዛ ብቅ ሳትል ገና ጥንት፦

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

ፍቅሬ አንቺ የፈርፈር ሽቶ፣
አንቺ የከረን ሎሚ፤
በይ ደህና ከረሚ።[11]

ሲል አንጎራጉሯል። ጥላሁን በተለያዩ ማህበረሰባዊ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶች በታጀቡ ዘፈኖቹ ቢመክር ቢዘክር ሰሚ በማጣቱ:-

ጨኸቴን ብትሰሙኝ፣
ይኸው አቤት አቤት እላለሁ፤
በደል ደርሶብኝ እጮሃለሁ፤
ችያለሁ።[12]

በማለት በብርቱ እስከመማጸንም ደርሶ ነበር። ጆሮ ዳባ ልበሱ በዝቶበት ነበርናም:-

አልጠፋልህ ብሎኝ የልቤ ውስጥ እሳት፤
ጥርሴ እንዲያምር ብዬ ተወጋሁ ንቅሳት።[13]

እያለ የውስጡን ጉዳት በጥርሱ መንፈቅፈቅ ከድኖት ለዘመናት ለኖረው ኢትዮጵያዊ አፈ-ሕዝብ ሆኖ አገልግሏል። የዚህ ጽሁፍ አድማስ ባለመፍቀዱ እንጂ ከላይ እንደተጠቆመው ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ድምፃውያን በባላባታዊው ስርዓት ውስጥ በግልጽ ይታዩ የነበሩትን አድልዖን፣ ጉቦን፣ በጾታና በጎሳ ምክንያት ይደርሱ የነበሩ ልዩነቶችን፣ ኋላ ቀርና ጎጂ ባህሎችን ወዘተ ወቅቱ የሚፈቅደውን ያህልና ድንገት የሚገኙ ጠባብ ቀዳዳዎችን በመጠቀም አልፎ አልፎም ረቂቅ የሆነ ጥበባዊ ችሎታን በመጠቀም የዘመኑን ብልሹ አስተዳደር ገስጸዋል፤ ሞግተዋል። ለ"ድፍረታቸው" ከፍተኛ ዋጋ የከፈሉም ጥቂቶች አይደሉም።

በኮሎኔል መንግስቱ ኃይለማርያም አገዛዝ ዘመንም እንዲሁ ኢትዮጵያውያን ድምጻውያን በወቅቱ በመንግስት ባለስልጣኖችና በመንግስታዊ ድርጅቶች ወይም ቡድኖች ጫና የተከወኑ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ድርጊቶችን አምርሮ ከመቃወም አልታቀቡም። የወታደራዊውን ስርዓት ፖሊሲዎች በኪነጥበብ መድረኮች ላይ እንዲያንጸባርቁ በስርዓቱ የተቋቋሙ የሙዚቃ ቡድኖች ሳይቀሩ ሕዝባዊ ወገንተኝነታቸውን ለመግለጽ የተገደዱባቸው ሁኔታዎች በወቅቱ ተከስተው ነበር። የከፋ ክፍለ ሃገር የፖሊስ ሰራዊት የሙዚቃ ኦርኬስትራ አባል የነበረው መክብብ የተሻ ወርቅ በ1979 እ.አ.አ. ባንድ ሕዝባዊ በዓል ላይ:-

የደርግ መኪና ሸራ የለበሰው፤
ተራማጁን ሁሉ ወዴት አደረሰው።[14]

እያለ በይፋ ካቀነቀነ በኋላ በመድረክም በአካልም ዳግም ሳይታይ ቀርቷል - አርዓያነቱ ዘላለማዊ ሆኖ ቢኖርም።

በዛሬይቱም ኢትዮጵያ ከያንያን የሃገራቸውን ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ጉዳዮች በሚመለከት የተቃውሞ ድምፃቸውን ከማሰማት ያልተገቱ ሲሆን አንዳንዶቹም ድፍረቶቻቸው ያስከተሏቸው አስከፊ ውጤቶች ሰለባ ሆነዋል። አቶ መለስ ዜናዊ ገና በሽግግር መንግስት መሪነት ላይ እያሉ ኤርትራ ከኢትዮጵያ ትገነጠል ዘንድ ለተባበሩት መንግስታት ደብዳቤ አቅርበውና መንግስታቸው ሳያሰልስ ልዩ ድጋፍና ትብብር አድርጎ የኢትዮጵያ አካል የሆነችው ኤርትራ ከእናት ሃገሯ ከኢትዮጵያ እንድትለይ ቢደረግም ወደፊት በሕዝቡ ግፊት መልሶ መገናኘት የማይቀር መሆኑን ሻምበል በላይነህ:-

አስመራ ሃምባሻውን ሕምብሽታውን ቋጥረን
ምፅዋ ዳሕላክ ላይ ሽርሽር ሄደን፣
እንገናኛለን፤ አመኑ አላመኑ

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

በርሊን ግንብ ፈርሷል እንኳንስ ድንኳኑ።[15]

እያለ አፈ-ሕዝብ ሆኖ ባደባባይ ከመጮሁ በተጨማሪ ድርጊቱን ጭምር "ታሪክ ይፍረደው" እያለ የወገኑን ብርቱ ሃዘን ገልጦበታል። እንደሻምበል ሁሉ ብዙዎች ሌሎች ኢትዮጵያውያን ድምጻውያንም በተመሳሳይ መልኩ የወገኖቻቸውን መከራና ስቃይ ባደባባይ የማስተጋባት ልዩ ሚና ተጫውተዋል። ከኢትዮጵያ ሕዝብ አብራክ የተገኙ ናቸውና በተለያዩ ወቅቶች የተከሰቱ አካባቢያዊና ብሄራዊ ጉድፎች እየነቀሱ መልሰው ለሕዝባቸው በማሳየት መስታወቱ ሆነው የኖሩትን ያህል ግንባር ቀደም ሃላፊነትን ተቀብለውና አፈ-ሕዝብ ሆነው ባደባባይ የወገናቸውን ለቅሶ ሲያለቅሱ፤ ህመሙን ሲታመሙ፤ እርዛቱን ሲታረዙ፤ ረሃቡን ሲራቡና ጥማቱን ሲጠሙ ድርብ ስቃይና መከራን ለመኖር ተገደዋል።

# የቴዲ አፍሮ የተቃውሞ ዘፈኖች

ከላይ እንደተጠቀሰው ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ድምፃውያን የየዘመኑን የወገናቸውን ብሶት በድፍረት ባደባባይ የማስተጋባት ልዩ ሚና ተጫውተዋል፤ ለ"ድፍረታቸው"ም ልዩ ዋጋ ከፍለዋል። ቴዲ አፍሮ የዚህ ብሔራዊ ሚና ተጫዋቾችን ክበብ በቅርቡ የተቀላቀለ ሲሆን ለ"ደፋሮቹ" በተዘጋጀ ወጥመድ ውስጥ አውቆ የገባ፤ ድርጊቱም የሚያስከፍለውን ከፍተኛ ዋጋ ለመክፈል ራሱን በመስዋዕትነት ያቀረበ አዲሱ ፋና ወጊ ነው።

ቴዲ አፍሮ በቅርቡ በመኪና ግጭት አንድ ኢትዮጵያዊ በድለሃል ከመባሉ አስቀድሞ ወገኖቹን ክፉኛ የበደሉትን የወቅቱን የሃገሪቱን ያገዛዝ ስርዓት አራማጆች፦

በአስራ ሰባት መርፌ በጠቀመው ቁምጣ
ለለውጥ ያኰፈረው ዙፋን ላይ ሲወጣ ፤
እንዳምናው ባለቀን ያምናውን ከቀጣ፤
አዲስ ንጉስ እንጂ ለውጥ መቼ መጣ።[16]

በማለት በድፍረት ተቃወመ። በደል ከተባለ ሕዝብ ሃገርና ትውልድ ይቅር የማይሉት ግዙፍ በደል በሃገሩ ላይ እየዘነበ መሆኑን አስቀድሞ ባደባባይ አጋለጠ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ለተከታታይ የበደል ስርዓቶች መዳረጉ ክፉኛ ቆጭቶታልና፦

ይኸ በክፉ ቃል ይኸንን ሲወቅሰው፤
ይኸ በጥላቻ ይኸንን ሲወቅሰው፤
መለየት አቃተን የሚበጀንን ሰው።[17]

እያለ በወገኖቹ በዳዮች ላይ ተሳለቀ። የጭካኔያቸውን አድማስ ለማሳየትም፦

አቤት ስቃይ... አቤት ጠኔ...ሰማይ ጨከነ በወገኔ፤
ስንት አሳለፍን አልቅሰን ...ሳናባራ ብለን ወይኔ።[18]

እያለ በምሬት ተከታታዮቹን የበደል ስርዓቶች በይፋ ኮነነ። ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ዳር ዳር የሚዞሩትን ብሔራዊ ጉዳይ ደፍሮ ተጋፈጠ። የዕድሜ አቻዎቹ ጉልበቱ ባጠጣቸው ወቅት ድንገት ብቅ ብሎ በጠራራ ፀሐይ "አልነጋም ወይ ሌቱ"ን ዘመረ። አዛውንት እናትና አባቶች "የአዲስ ትውልድ ያለህ" እያሉ በሚጮሁበት ወሳኝ ወቅት ሳይጠበቅ ብቅ ብሎ ራሱን ለመስዋዕትነት አቀረበ። እንደቅጠል ለሚረግፉ ወንድምና እህቶቹ ሳይቀር፦

እዚህ ጋ ደግሞ ሌላ ትከሻት፤
ወገኔ አለቀ በወሲብ እሳት።[19]

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

**እያለ ለሚሊዮኖች በአደባባይ ብቻውን አነባ። ለቅሶ ዋይታቸውን አስተጋባ።**

**ቴዲ ሰርክ ብዙዎች ለብቻቸውና በየስርጓጉጡ በድብቅ የሚያነበንቡትን እውነት አደባባይ ይዞት ወጣ። መሰረታዊውንና ብሔራዊውን የኢትዮጵያውያን የጋራ ችግር መፍቻ ቁልፉ የሕዝብ አንድነትና የሃገር ሉዓላዊነት መሆኑን ለማሳየት የፍቅር እጦት ነው ችግሩ ሲል በይፋ ገሰጸ።**

ፍቅር አጥተን እንጂ በራብ የተቀጣን፤
አፈሩ ገራገር ምድሩ መች አሳጣን፤[20]

**እያለም ወገኑን ተማጸነ። ወገን ከወገኑ በፍቅር እንዲስማማ ያስታራቂ ብድር ለመሻት ሁሌም ወደ ባዕድ ከመሮጥ ይልቅ:-**

በተስፋዋ መሬት እንዲፈጸም ቃሉ
ሞፈሩን ያዙና ይቅር ተባባሉ።[21] **እያለ መከረ፤ ዘከረ።**

**ቴዲ ለረጅም ዓመታት ብዙዎች ሃገር በቀል ባለልምዶችና ባለዕውቀቶች ሲወተውቱት የኖሩትን "ያገሩን ሰርዶ ባገሩ በሬ" የሚለውን የቆየ ሃገራዊ ጥሪ እንደገና ድምጹን ከፍ አድርጎ አሰማ። እግረመንገዱንም ጥላቻ ለራስም ለወገንም የሚኖረውን ከፍተኛ አደጋ ለመጠቆም:-**

እስቲ ተዋደዱ ይያያዝ እጃችሁ ... በልዩነታችሁ፤
አለበለዚያማ በምን ያስታውቃል ... እኛን መውደዳችሁ።[22]

**በማለት ፍቅርን ወንድምና እህትነትን ማስቀደም እንደሚያሻ በግልጽ ሰበከ። ቴዲ ከመለያየት ይልቅ አንድነትን የሚመኝ ነውና:-**

ይቅር በለንና የበደለን ወቅሰን፤
ወረታ አስተምረን አንድ አርገን መልሰን።[23]

**እያለ አምላኩን ጭምር ተማፀነ። በብሔራዊና ሃገራዊ ችግር ብቻውን በገነ። የልጅ አዋቂ ሆኖና በአርቆ አስተዋይነት ጭምር:-**

ቂም በቀል ከፋ ነው ካምላክ ያለያያል፤
ሰው አርጎ መትጋት ግን ከቅጣት ያስተሠርያል።[24]

**ሲል የሃይማኖታዊ ስነምግባርን ግዴታ የመወጣት አስፈላጊነት ጭምር በግልፅ ለፈፈ። የቴዲ አፍሮ ዘፈኖች ዋነኛ ማሳረጊያና ማሰሪያ ቃሉ ለሃገሩና ለወገኑ ያለው የወደፊት ብሩኅ ተስፋ መሆኑም ልዩ ያደርገዋል።**

ዘሰዓት ለኢትዮጵያ ወደተስፋ ጉዞ፤
ባሕሩን ሚያሻግር አንድ ሙሴ ይዞ፤
ቅርብ ነው አይቀርም የኢትዮጵያ ትንሳዔ፤
ባንድነት ከገባን የፍቅር ሱባዔ።[25]

**የሚሉት አንጓ ስንኞቹ በሃገሩና በወገኑ በጭራሽ ተስፋ የማይቆርጥ ለመሆኑ በቂ ምስክሮች ናቸው። ቴዎድሮስ ካሳሁን ለዘመናት አይነኬ የሆነውን ሃይማኖታዊ መስክ ሳይቀር:-**

ተዋዶ ያለበት ... እስላም ክርስቲያኑ፤
ተዘነጋሽ እንዴ ኢትዮጵያ መሆኑ፤
አንቺም ባይማኖትሽ እኔም ባይማኖቴ፤
አብረን እንኖራለን አይጠበንም ቤቴ።[26]

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

እያለ ለብዙ ዘመናት ተግባብቶና ተከባብሮ የኖረውን ኢትዮጵያዊ ዜጋ ብሔራዊ ፍቅር በዘፈኖቹ አጉልቶ አሳይቷል። ቴዎድሮስ ካሳሁን ባስቀረጻቸውና ለሕዝብ ባሰራጫቸው ዘፈኖቹ በተለይ ለሃገር አንድነት ለሕዝብ ሉዓላዊነትና ለማናቸውም የሰብዓዊ መብቶች መከበር ልዩ ትኩረት መስጠቱ የድምጻዊውን አርቆ አስተዋይነት ብቻ ሳይሆን ለኢትዮጵያም ሕዝብ የወደፊት ዘላቂ ሰላምና የተረጋጋ ሕይወት ዋነኞቹን አስፈላጊ ቁልፍ ጉዳዮች ለመጠቆም አስችሎታል።

ሃዋርድ ዚን (2006፡ 232) የተባለ ታዋቂ የጥበብ ሰው የተቃውሞ የኪነጥበብ ስራዎችን ዋነኛ ዓላማ ባጭሩ ሲያብራራ "all protest literature says to the reader, 'have hope - you are not alone." ሲል ገልጾታል። ቴዲ አፍሮም በቅርቡ ባስቀረጻቸው ዘፈኖቹ ጥልቅ መልዕክቶች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ተስፋ ሰጪ የመሆኑን ያሕል ለራሱም ያለጥርጥር ቀደም ካሉ ዘመናት ጀምሮ የሚመጣባቸውን ሁሉ ለመቀበል ድፍረትን ካሳዩ ኢትዮጵያውያን የኪነጥበብ ሰዎች ጎራ ለመቀላቀል አስችሎታል። ቴዲ በዘፈኖቹ አማካኝነት የደረሰበትን ለመቀበል ያሳየው ግዙፍ መስዋዕትነት ሕዝባዊ ከያኔነቱን በግልጽ ከማሳየቱም በላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዘመናት ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትሕ ያደረገውና ዛሬም በማድረግ ላይ ያለው ሕዝባዊ ትግል እንዲቀጥል አንድ ራሱን የቻለ በቂ ምክንያት ብቻ ሳይሆን እንዲቀጣጠልም ጭምር ልዩ እገዛ ያደርጋል።

## ጣጠቃለያ

በዝርው በግጥም ወይም ሁለቱንም መልኮች ባካተተው በድራማ መልክ የሚቀርቡ የኪነጥበብ ስራዎች ጥበብ ሊባሉ የሚበቁት በሚያሳዩት ልዩ ያቀራረብ ስልት ብቻ ሳይሆን ለተደራሲዎቻቸው በሚፈነጥቁት ይዘትም ጭምር ነው። ዘፈንንም የሚያጠቃልለው የተቃውሞ የኪነጥበብ ስራ ዋና መነሻው ያንድ ወቅት የፖለቲካ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ኑሮ ፖሊሲ ወይም ድርጊት በመሆኑ ፖሊሲውን ወይም ድርጊቱን የሚያንጸባርቅ ስራ እንዲፈልቅ ምክንያት ይሆናል። መጤዎቹ የደቡብ አፍሪካ ቅኝ ገዢዎች በሌሎች የዓለም ክፍሎች ጨርሶ ታይቶ ባልታወቀ መንገድ ቅጥ ያጣ የዘረኝነት ፖሊሲ አውጥተው የሃገሪቱን ነዋሪ ጥቁር ዜጎች ለዘመናት በጭቆና ቀንበር ስር እንዲማቅቁ ባደረጉበት በሃያኛው ክፍለዘመን መባቻ ለአፓርታይድ ፈላጭ ቆራጭ ፖሊሲዎች ጨርሶ ያልተንበረከኩ የኪነጥበብ ሰዎች እንዲፈጠሩና ጥቁር አፍሪካውያኑ ወገኖቻቸው ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትሕ ያደርጉት የነበረውን ትግል ሳያሰልሱ በተቃውሞ ጽሁፎቻቸው እንዲያግዙ ምክንያት ሆኗል። በዚያ አስከፊ ስርዓት ውስጥ የተፈጠሩት ደቡብ አፍሪካውያን የኪነጥበብ ባለሙያዎች እንደሌሎች የሃገሪቱ ዜጎች በትግሉ የሰርክ ተሳትፎ ከማድረግ በተጨማሪ ባቀረቧቸው ያልተቋረጡ የተቃውሞ ድርሰቶች አማካኝነት ለትግሉ ልዩ ድጋፍ አድርገዋል። ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ ካትሊንና ራልፍ (1991፡176) እንደሚከተለው ጽፈዋል።

The policy of apartheid in South Africa has stimulated a long tradition of protest literature, beginning early in the twentieth century with Solomon T. Plaatje's Native Life in South Africa and including the work of both white and black writers: Novels, Plays, and Short stories, such as Alan Paton's Cry the Beloved Country, Peter Abraham's A Night of Their Own, Doris Lessing's Children of Virtue, Nadine Gordimer's Something Out There, Alex La Guma's In the Fog of The Season's End, Gibson Kente's Too Late, and Mthuli Shezi's Shanti; and poetry by Mongane Serote, Njabulo Ndebele, Mandlenkosi Langa, Mafika Gwala, James Mathews, and Don Mattera.

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

እንደደቡብ አፍሪካ ሁሉ በአሜሪካም ጥቁር ሕዝቦች ከባርነት ቀንበር ተላቀው ለነጻነትና ለእኩልነት ባደረጉት መራራ ትግል አያሌ የጥበብ ሰዎች በተቃውሞ ጽሁፎቻቸው አማካኝነት ለትግሉ ከፍተኛ እገዛ አድርገዋል፤ በሂደቱም የተከፈሉትን ግዙፍ መስዋዕትነቶች ታሪክ ክቡር ስፍራ ሰጥቷቸዋል። በዚህ ዘርፍ ሳይጠቀሱ መታለፍ የሌለባቸውን አፐተን ሲንክሌር (1996፡ 48) የተባለ የስነጽሁፍ ሰው ሲገልጽ፡-

Some of the most famous protest literature in the world has its roots in American history... some great American authors of protest literature include Thomas Paine, Thomas Nast, John C. Calhoun, and Martin Luther King. Through eloquent, sometimes subtle means, these authors became the spokesmen for their particular protest movements. ሲል ጽፏል።

በተለይ ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ በትግሉ ዘርፍ ለተቃውሞ ስነጽሁፍ የሰጡትን ከፍተኛ ግምትና ልዩ ስፍራ ሲክሌር (1996፤ 49) ሲጠቁም፡- Martin Luther King can be said to have been an important player in the forum of protest literature. A crusader for black civil rights, King had three plans for achieving complete black equality. Literature comes in during King's third segment, known simply as "Plan C". በማለት አብራርቷል። ጥቁር ሕዝቦች በደቡብ አፍሪካና ሰሜን አሜሪካ ለነጻነት ባደረጉት መራራና ረጅም ትግል የተቃውሞ ስነጽሁፍ እንደአንድ ከፍተኛ የትግል መሳሪያ ማገልገሉ ኪነጥበብ በሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ያለውን ከፍተኛ ቦታ በግልጽ የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን ጥበቡ የሰው ልጆች ሰብዓዊ ግብር ውጤት ለመሆኑ ማረጋገጫም ጭምር ነው።

በኢትዮጵያ የተለያዩ ደራስያን ለረጅም ዓመታት በየወቅቱ የተመለከቷቸውን እኩይ መንግስታዊ ፖሊሲዎችና ድርጊቶች በድርሰቶቻቸው ውስጥ በማቅረብ አጥብቀው የተቃወሙ ቢገኙባቸውም በቀጣይነት የሕዝብን ትግል ለማገዝ የሚያስችሉ የተቀነባበሩ ጥረቶች አለመታየት ጥቂቶች ብቻ የግንባር ስጋ እንዲሆኑና ተነጥለው እንዲመቱ አስችሏል። በትናንትናው የኢትዮጵያ የኪነጥበብ ታሪክ ሂደት በግልጽ የታየው የተቃውሞ ድርሰት አምራቾችን እየነጠሉ የማሳደድ፣ የማስር፣ የማጋዝ ብሎም ደብዛቸውን የማጥፋትና የመግደል ድርጊቶች ዛሬም በቴዲ አፍሮና በሌሎች ላይ ተግባራዊ እየሆነ መቀጠሉ ሊያሳስብና መፍትሔ ሊፈለግለት የሚገባ ጉዳይ ነው። በደቡብ አፍሪካ በሰሜን አሜሪካና ሌሎችም ሃገሮች ውስጥ በተቀነባበረና ቀጣይነት ባለው መልክ የሕዝብን ትግል በበቂ ማገዝ የቻሉ ስራዎች እንደታዩ ሁሉ በኢትዮጵያም የተቃውሞ የኪነጥበብ ስራዎች በብርቱ ሊታገዙና ለነጻነት ለእኩልነትና ለፍትሕ የሚደረገውን ትግል በበቂ እንዲያግዙ መደረግ ይኖርበታል። ካለበለዚያ ቴዲ አፍሮ በትክክል እንዳስገነዘበው:-

አይቶ በዝምታ በስተመጨረሻ፤
መጮህ ምን ያደርጋል ጀብ ከሄደ ውሻ።[27]

እንዳይሆን አስቀድሞ ማሰቡ ጥቅሙ ለሃገርም ለወገንም ነው። ሃገርና ወገን የግንባር ስጋ የሚሆኑትን ተቃዋሚዎቹን እያጣ በሄደ ቁጥር ሁሉንም አሜን ብሎ ተቀባይና ለህሊናው ሳይሆን እንደእንስሣ ለሆዱ የሚያድር ዜጋ እንዳይበረክት ያሰጋል። የኢትዮጵያን የወቅቱን ሁኔታ በጥሞና ያጤነው ቴዲ አፍሮ "ያስተሠርያል" ማለቱ የዚሁ ከፍተኛ ፍራቻ ተጋሪ በመሆኑ ነው። ያስተሠርያል - አዎን፤ ሞትም ባገር ያምራል።

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

# ማስታወሻዎች

1 አፈሩን ያቅልልላቸውና ክቡር ሎሬት ፀጋዬ ገብረ መድህን ቀዌሳ በኢትዮጵያ ሥነፅሁፍ ታሪክ በተለይም የተቃውሞ ድርሰቶችን በማቅረብ በኩል ልዩ ሥፍራ የሚሰጣቸው ገጣሚ ባለቅኔና ፀሐፌ ተውኔት ነበሩ። በአብዛኛዎቹ ስራዎቻቸው ስለኢትዮጵያዊነት ስለሃገር ፍቅርና አንድነት ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ከማሰማትም ባሻገር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ኢኮኖሚና ማኅበራዊ ኑሮ ዘርፍ የሚታዩ ጉዳዮችን እያነሱ በድፍረት በፈጠራ ስራዎቻቸው አማካኝነት ቀስቅሰዋል፤ አስተምረዋል። በሦስቱም ስርዓቶች ማለትም በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በወታደራዊ ደርግና በህወሓት/ኢሕአዴግ ዘመን ለመኖር የታደሉ በመሆናቸው አንኳር አንኳር ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ የታዩ ጉድፎችን ለመንቀስ በብርቱ ለመድከማቸው ለትውልድ ትተዋቸው የሄዱት ስራዎቻቸው ገሃድ ምስክሮች ቢሆኑም ሰሚ ጆሮ ማጣታቸውን ግን ሳይደብቁ በተጠቀሱት ስንኞች አማካኝነት ገልጠዋል።

2 ባሁኑ ወቅት ድምጻዊ እከሌ ከማለት ይልቅ አርቲስት እከሌ እያሉ መጥራት እየተለመደ መጥቷል፡፡ ነገር ግን አርቲስት የተውሶ ቃል ነውና ድምጻዊ ማለቱ የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል - “ሳይቸግር ጤፍ ብድር” እንዳይሆን።

3 ይህ ፅሁፍ ምንም እንኳ በድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን የተቃውሞ ዘፈኖች ይዘት ላይ ቢያተኩርም በመኪና አደጋ ሕይወታቸው አልፏል የተባሉትን (ሆነም አልሆነ) ኢትዮጵያዊ በእኩል ዓይን የሚመለከት መሆኑን መግለፁ አግባብነት አለው።

4 ይህ ጽሁፍ “ተቃውሞ በአማርኛ ስነፅሁፍ ውስጥ” በሚል ርዕስ ወደፊት ለሚዘጋጅ (እስካሁን ተዘጋጅቶም ከሆነ እሰየው) ሰፊ ጥናት እንደእንጎቻ ሆኖ ሊያገለግል ይችላል። የተቃውሞ ስነጽሁፍ ራሱን የቻለ አንድ የስነጽሁፍ ዓይነት ሆኖ መቆጠር ከጀመረ ሰንብቷል። እንዳውም በሰለጠኑት ሃገሮች ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በሚገኙ የስነጽሁፍ ተቋማት እንደአንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል።

5 ትውፊት Falklore የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ተክቶ ማገልገል ከጀመረ ቆይቷል። የአንድ ሃገር ሕዝብ ትውፊት ሲባል ስነቃልን፣ (Oral Literature) ባህላዊ ኪነትን፣ (Performing Falk Art) ማህበራዊ ልማድን፣ (Social Falk Custom) እንዲሁም ቁሳዊና ህሊናዊ ባህልን (Material and Ideal Culture) የሚያካትት ነው።

ስነቃል ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የኖሩትን እንደ ተረት፣ አፈታሪክ፣ እንቆቅልሽ፣ ብልግር (ብልህነት የተሞላበት አነጋገር) (Fable) ምሳሌያዊ አነጋገሮች ወዘተ

ባሕላዊ ኪነት የምንለው እንደእስክስታ፣ ረገዳ፣ ጭፈራ፣ ሆያ ሆዬ፤ አበባየሆሽ ወዘተ በየብሄረሰቡ በአውዳመትም ሆነ በሌሎች ወቅቶች በተግባር የሚከወኑ ኪነታዊ እንቅስቃሴዎች...ወዘተ

ማህበራዊ ልማድ የምንለው የልዩ ልዩ ያገራችን ብሄረሰቦች የሚፈጽሟቸውና የሚከተሏቸውን ዓይነት ልማዶች ለምሳሌ አቴቴ፣ አድባር፣ ወዘተ

ቁሳዊ ባሕል ደግሞ በሃገራችን በየብሔረሰቡ ለልዩ ልዩ የዕለት ተዕለት ተግባራት ለጠቀሜታ የሚውሉ ቁሳቁሶችን ለምሳሌ እንደሞፈር፣ ቀንበር፣ ማሰሮ፣ መግላሊት፣ ወጨት...ወዘተ

ህሊናዊ ባሕል የምንለውም ለምሳሌ አዲስ ቤት ሲሰራና ሲገባ፤ ትዳር ሲመሰረት፣ ልጅ ሲወለድ፣ ክርስትናን ወይም እስልምናን በመቀበያ ጊዜ፣ ማዕረግ ሲገኝ፣ ወዘተ እንደየብሄረሰቡ ባሕል ሰዎች በቃል የሚለዋወጧቸው የንግግር ቅብብሎሽ...ወዘተ ያጠቃልላሉ። የየሃገሩ ትውፊት የየሃገሩ መገለጫና የየሃገሩ ቅርስና ሃብትም ጭምር ነው።

ስለትውፊት የተሰነዘረው አጭር ማብራሪያ የጽሁፉ አዘጋጅ የቀለም አባት የሆኑት ገጣሚውና ባለቅኔው ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬው በ1983 እ.አ.አ. ክፍል ውስጥ ካቀረቡት ዕለታዊ የስነቃል ትምህርት የተቆነጠረ ነው።

6 የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስርዓቶችም ሆነ የስርዓቱን አራማጆች እኩይ ድርጊቶች በኪነጥበባዊ ስራዎቻቸው በይፋ በመቃወም ረገድ አያሌዎች ተጠቃሾች ቢኖሩም ተክለሃዋርያት ተክለማርያምን፣ ተሰማ እሸቴን፣ አቤ ጉበኛንና ፀጋዬ ገብረመድህንን በዓሉ ግርማን ሰይፉ መታፈሪያ ፍሬውን ለአብነት ያሕል በግርጌ ማስታወሻም ላይ ቢሆን መጠቅሱ ተገቢ ነው።

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

7 ይህ ግጥም ደራሲው በውል ባይታወቅም በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍል በተዘጋጀው "አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ" የማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ተጠቅሶ ተገኝቷል።

8 ዝኒ ከማሁ።

9 ከዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ የግል ማስታወሻ የተገኘ ግጥም። ደራሲው በውል ያልታወቀ።

10 "ምኞቴን ማን ያውቃል" በሚል ርዕስ ከቀረበው የብዙነሽ በቀለ ዘፈን የተቀነጨበ።

11 "በይ ደህና ክረሚ" ከተሰኘው የጥላሁን ገሰሰ ዘፈን የተቆነጠረ።

12 "ጨኸቴን ብትሰሙኝ" በሚል ርዕስ ከቀረበው የጥላሁን ዘፈን የተወሰደ።

13 "መሳቁን ይስቃል" ከተሰኘው የጥላሁን ዘፈን የተቆነጠረ።

14 መክብብ የተሻ ወርቅ እ. አ. አ. 1979 ጅማ ከተማ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት ለሜይ ዴይ በዓል በቀረበ ዝግጅት ላይ ካቀረበው የዘፈን ግጥም ውስጥ በዚህ ጽሁፍ አዘጋጅ አዕምሮ ተቀርጾ የቀረው ዓቢይ ስንኝ ይህ ብቻ ነው።

15 ሻምበል በላይነህ "ኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ ካሳተመው ሲዲ የተወሰደ።

16 ከቴዲ አፍሮ "ያስተሠርያል" ሲዲ የተወሰደ።

17 ዝኒ ከማሁ።

18 ዝኒ ከማሁ።

19 ዝኒ ከማሁ።

20 ዝኒ ከማሁ።

21 ዝኒ ከማሁ።

22 ዝኒ ከማሁ።

23 ዝኒ ከማሁ።

24 ዝኒ ከማሁ።

25 ዝኒ ከማሁ።

26 ዝኒ ከማሁ።

27 ዝኒ ከማሁ።

## ዋቢ መጻሕፍት

Aaron, Daniel. "The Radical Humanism of John Steinbeck: The Grapes of Wrath Thirty Years Later." *Saturday Review* 51 (1968) 26-7.

Adrian, Daryl. "Steinbeck's New Image of America and the American." *Steinbeck Quarterly* 3 (1970): 83-92.

"Assisting John Steinbeck." *Newsweek* 47 June (1956): 56.

Blotner, Joseph. *The Modern American Political Novel.*

Cannon, Gerald. "The Pauline Apostleship of Tom Joad." *College English* 24 (1962): 222-224.

Carpenter, Frederic. "The Philosophical Joads." *College English* 2 (1941): 315-25.

Chase, Richard. "Radicalism in the American Novel." *Commentary* 23 (1947): 65-71.

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions

Cook, Sylvia. “Steinbeck, the People, and the Party.” *Steinbeck Quarterly* 15 (1982: 11-23.

Howard Zinn (2006) American Protest Literature, The Belknap Press, USA.

*Kathleen Morner and Ralph Rausch (1991) Literary Terms, McGrow Hill, New York, N.Y*

ሻምበል በላይነህ (1997) ታሪክ ይፍረደው፣ ሲዲ፣ ናሆም ሬከርድስ፣ ዋሽንግተን ዲሲ፤ ዩ. ኤስ. ኤ.

ሻምበል በላይነህ (2000) ኢትዮጵያ፤ ሲዲ፤ ኢትዮንዝ፤ ዩ. ኤስ. ኤ.

ተስፋዬ ገብረአብ (2000) የጋዜጠኛው ማስታወሻ፣ Sunnyside Publishers, Pretoria, South Africa.

ቴዲ አፍሮ (2004) ያስተሠርያል፣ ሲዲ፣ ናሆም ሬከርድስ፣ ዋሽንግተን ዲሲ. ዩ. ኤስ. ኤ.

Upton Sinclair (1996) The Cry for Justice: An Anthology of the Literature of Social Protest, Barricade Books Inc. U.S.A.

Woodward, Robert, (1965) *The Social Rebel in American Literature*

This content downloaded from 213.55.95.158 on Sat, 11 Jan 2014 06:02:44 AM
All use subject to JSTOR Terms and Conditions